**Ethiopian Solidarity Movement**
የኢትዮጵያውያን ትብብር ንቅናቄ
info@ethiosolidaritymovement.org
Phone: +1 (202) 754-5328
https://www.ethiopiansolidaritymovement.org

# የኢትዮጵያውያን የትብብር ንቅናቄ የድጋፍ መግለጫ፤

## የኢትዮጵያውያን ዶክተሮችንና የሁሉም የጤና ሙያተኞችን ጥያቄዎች ተገቢነት በማመን በፍጥነት ሊመለሱላቸው ይገባል ይላል!!

ግንቦት 7, 2017 ዓ.ም.

ኢትዮጵያውያን የጤና ባለሙያዎች የሚያበረክቱትን ሙያዊ አገልግሎት የሚመጥን ደመወዝ፣ የጤና መድህን (ዋስትና) እና የተሻለ የሥራ ሁኔታን ነው የጠየቁት። ጥያቄዎቻቸውንም ያቀረቡት በሠላማዊ መንገድ ነው። ጥያቄዎቻቸው ትክክልና ተገቢ ናቸው፣ እያካሄዱት ያለው እንቅስቃሴም ተገቢ ስለሆነ የኢትዮጵያውያን የትብብር ንቅናቄ በሙሉ ልብ ነው የሚደግፋቸው። ሌሎች ኢትዮጵያዊ ማኅበራትና ድርጅቶችም ከጎናቸው እንዲቆሙ እንጠይቃለን።

ዶክተሮችና ሌሎች የጤና ባለሙያዎች እያደረጉት ያለው እንቅስቃሴ፣የሚሰጣቸው ደሞዝ ኢትዮጵያ ዛሬ በምትገኝበት ኢኮኖሚያዊና የኑሮ ሁኔታ በበቂ ሊያኖራቸው የማይችል መሆኑን፣ የጤና መድህን (ኢንሹራንስ) እንደሌላቸውና እንደሚያስፈልጋቸው፣ የሚሠሩባቸው ሁኔታዎችም ምቹ እንዳልሆኑ ፍንትው አድርገው አሳይተዋል። በርግጥም የሚኖሩበትና የሚሠሩበት ሁኔታዎች ሳይሟሉላቸው ሕዝቡ ከነሱ ሊያገኝ የሚገባውን አገልግሎት አሟልተው ሊሰጡ አይችሉምና ሙያቸውንና ክብራቸውን በሚመጥን ደረጃ ሊከፈላቸውና የጠየቁት የጤና ዋስትና እና የተሻለ የሥራ ሁኔታም ያለአንዳች ማቅማማት ሊሟላላቸው ይገባል እንላለን።

የኢትዮጵያ ህዝብ በየተሠማራበት የሥራ መስክ የሚከፍለው ቀረጥ የህዝቡን ሠላምና ደህንነት፣ እንዲሁም የህክምናና የትምህርት አገልግሎቶች በዋናነት ካላሟላ ታዲያ ለምን ብሎ ነው ሁሉም አምራችና በሥራ ላይ የተሰማራ ዜጋ ከገቢው እየቆረጠ ጀርባው እስከሚጎብጥ ዕዳ ያለበት ይመስል የሚቀፈቅፈው? የገዥዎችን ቅምጥል ኑሮ ለማሟላት ሊሆን አይገባም። ወይንም ለዜጎች ዕልቂትን፣ ለሀገርም ውድመትን እያመጣ ያለውን ማባሪያ የሌለው ጦርነት ማስቀጠያም ሊሆን አይገባም እንላለን። ከህዝቡ የሚሰበሰብ

**Ethiopian Solidarity Movement**
**የኢትዮጵያውያን ትብብር ንቅናቄ**
**info@ethiosolidaritymovement.org**
**Phone: +1 (202) 754-5328**
**https://www.ethiopiansolidaritymovement.org**

ማንኛውም ገንዘብ ለህዝቡ አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ፍላጎት ማሟላትና ተቋማቶችንም መገንባት ላይ ነው ሊውል የሚገባው።

ኢትዮጵያውያን ሀኪሞችና የጤና ባለሙያዎች ዛሬ እያደረጉት ያለው እንቅስቃሴና ትግል ለረጅም ጊዜ ሲጠራቀሙና ሲቆለሉ ከኖሩ ብሶቶች የመነጬ ናቸው። ዛሬ ሊቋቋሙት በማይችሉት የኑሮ ሁኔታ ውስጥ በመግባታቸው ነው ከእንግዲህ ይበቃል ብለው ደንታ-ቢሶች ሆነው ሲሳለቁ የቆዩትን የመንግሥት ባለሥልጣናት ሊታገሏቸው የተነሱት። ሀገራችን በብልጽግና ስም በተሰባሰቡት አምባገነኖች እጅ እየዳሸቀች ባለችበት ሁኔታ፣ ባለሥልጣናቱ ስለምናባዊ ዕድገትና ልማት ሲቀባዥሩ መዋላቸውን እንጂ ስለ ሕዝቡ ኑሮና ስቃይ ለደቂቃ እንኳን የሚያስብ ኅሊና እንደሌላቸው ደግመው፣ ደጋግመው አረጋግጠዋል።

ኢትዮጵያውያን ዶክተሮችና የጤና ባለሙያዎች እንቅስቃሴያቸውን በተቀነባበረ መንገድ በማኅበራዊ መገናኛዎች እያካሄዱ ናቸው። ለጥያቄዎቻቸው በአፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ጠይቀዋል። እንቅስቅሴው በኢትዮጵያ የጤና ባለሙያዎች ማህበር የተደገፈም ነው።

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑት ሸቀጦችና የፍጆታ ዕቃዎች ዋጋ እጅጉን እየተወደደ ስለመጣ ለማንኛውም ደሞዝተኛ ኑሮ ከብዷል። ለስድስት ዐመታት ሰፋ ባሉ የሀገራችን አካባቢዎች አውዳሚ ጦርነቶች፣ ዘር-ተኮር ግድያና ጭፍጨፋዎች፣ ማፈናቀልና ማሳደዶች፣ ዕገታዎችና በባንኮች በኩል የሚተላለፉ አስገዳጅ-ክፍያዎች፣ ... ሌሎችም ህገ-ወጥ ተግባሮች በባለሥልጣናቱ ዕይታ ስር እየተካሄዱ ናቸው። ሰላም ከሌለ አምራቹ ዜጋ ተረጋግቶ፣ ግብዓቶችን ሊያገኝና የምርት ተግባሮችንም በወቅቱና ባግባቡ ሊያካሄድ አይችልም። አምራቹ ዜጋም ከፊሉ በጦርነት እየተማገደ የመሞትና አካል-ጉዳተኛ የመሆን ዕጣው ሠፊ ነው። ስለሆነም የምርት እድገትና ልማት ሊገኝ የሚችልበት ሁኔታ ጠባብ ነው። እንዲያውም በተከታታይ ለአያሌ ዐመታት የምርት እጥረት ነው ያለው። የባለሥልጥናቱ ዐይን ያወጣ ክህደትና ዕብለት ዕውነታውን አይለውጠውም። ታዲያ ምርት እያሽቆለቆለ፣ የሸቀጦች ዋጋም እየጋሸበ ባለበት ይባስ ብሎ የብርና-ዶላር ምንዛሬ

Ethiopian Solidarity Movement
የኢትዮጵያውያን ትብብር ንቅናቄ
info@ethiosolidaritymovement.org
Phone: +1 (202) 754-5328
https://www.ethiopiansolidaritymovement.org

እንዲንሳፈፍ ሲደረግ፣ የብር የመግዛት አቅሙ በግማሽ ያህል መውደቁ፣ ደሞዝተኞች የበፊቱ ደሞዛቸው ቢያንስ በዚያው ልክ በእጥፍ ሊያድግ በተገባው ነበር።

ሌላው የመኖሪያ ቤት ጉዳይ ነው። አዲስ አበባና ሌሎችም ከተማዎች ውስጥ መኖሪያ ቤቶችን በማን አለብኝነት የብልጽግና ባለሥልጣናት በማፈራረስ ላይ ስለሆኑ፣ ሀኪሞችና የጤና ባለሙያዎችም እንደሌሎቹ ዜጎች ቤት-አልባና ተሳዳጆች ተደርገዋል። የብልጽግና ባለሥልጣናት በዘር-ጥላቻ፣ በዕውቀት ማነስ፣ በእብሪት የታወኩ በሚመስል አካሄድ እየተደናበሩ ስለሆነ ሰከን ብለው ማሰብና ዛሬ እየተፈጠረ ያለውን እጅግ አስጊ የሆነ የሁለንተናዊ ቀውስ ሁኔታ መገንዘብ ካልቻሉ፣ ጥሩውን ነገር ሁሉ አጥፍተው እነሱም ጠፊዎች ነው የሚሆኑት።

የኢትዮጵያ ዶክተሮችና ሌሎች የጤና ባለሙያዎች ጥያቄ በፍጥነት በሙሉ ሊመለስ ይገባል እንላለን። ጥያቄዎቻቸው ግልጽና በትክክል የቀረቡ ናቸው።

እነሱም፣-

1ኛ) ሙያቸውንና ግልጋሎታቸውን የሚመጥን ክፍያ እንዲሰጣቸው፣

2ኛ) የጤና መድኅን (ኢንሹራንስ) እንዲኖራቸው፣

3ኛ) የተሻለ የሥራ ሁኔታና በሳምንት ውስጥ ከ45 ሰዓቶች ያልበለጠ የሥራ ጊዜ፣ከዚያ እላፊ መሥራት ከተገደዱ ደግሞ፣ የሚመጣጠን ተጨማሪ ክፍያ እንዲሰጣቸው፣

4ኛ) ለስራቸው ምቹ የሆኑ የመኖሪያ ቤቶች ወይንም ድጎማዎችና፣ ለአደጋ የማያጋልጡ የመጓጓዣ ግልጋሎቶችም ስለሚያስፈልጋቸው እንዲሟሉላቸው ጠይቀዋል፣

5ኛ) ዶክተሮችና የጤና ባለሙያዎች በባለሥልጣናትና የጸጥታ ሠራተኞች ለሚደርሱባቸው በደሎችና ጉዳቶችም ተጠያቂነት እንዲኖር ጠይቀዋል፤

6ኛ) የህክምና ተቋማት አስድተዳደርና ምደባም ግልጽነት ያለው፣ዕውቀትንና ችሎታን ያገናዘበ፣ተአማኒነት ፍትሃዊነትና ተጠያቂነት የሰፍነበት እንዲሆን ጠይቀዋል።

info@ethiosolidaritymovement.org
Phone: +1 (202) 754-5328
https://www.ethiopiansolidaritymovement.org

የኢትዮጵያውያን የትብብር ንቅናቄ የዶክተሮችንና የጤና ባለሙያዎችን ጥያቄ የሚመለከተው በከፍተኛ ደርጃ ነው። ከእነሱ በፊት የኢትዮጵያ መምህራን በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ለዓመታት ተመሳሳይ የደሞዝ ዕድገትና የሚገባቸውን ደሞዝ እንኳን በወቅቱ እንዲያገኙ ጥያቄዎች በማቅረባቸው እስከ ድብደባና እስራት የደረሱ ግፍና በደል እንደ ተፈጸሙባቸውና እስከዛሬም ምንም ተጠያቂነት አለመኖሩን በምሬት ነው የሚያስታውሰው።

ሌሎች ሙያተኞችና ሁሉም የሀገሪቱ ሠራተኞችም የተዳፈኑትን ጥያቄዎቻችውን ከዶክተሮችና የጤና ባለሙያዎች ጋር ተባብረው ቢያነሱ ምን ሊፈጠር እንደሚችልም የኢትዮጵያውያን የትብብር ንቅናቄ ይገነዘባል። ሁሌም ሁሉንም በሃይልና በጉልበት ለማንበርከክ ከመሯሯጥና ወገንን ለዕልቂት፣ ሀገርንም ለጥፋት የዳረገው የብልጽግና መንግሥት ከግንዛቤም፣ከዕውቀትም፣ ከኅሊናም የተጣላና የራቀ በመሆኑ፣ በዶክተሮችና ሌሎች የጤና ባለሙያዎች ላይ አንዳች ጉዳት እንዳያደርስ አበክረን ለማስጠንቀቅ እንወዳለን። ጥያቄዎቻቸው ተገቢ የሆኑና አስቸኳይ ምላሽ የሚሹም ስለሆኑ፣ ባስታወቁት መሠረት ወደሙሉ ስራ ማቆም ትግበራ ከመግባታቸው በፊት ለጥያቄዎቻቸው በአፋጣኝ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል። ችግሮቹን በመካድ፣ ጠያቂዎቹን በማስፈራራትና በአፈና ችግሮቹን ልታዳፍኗቸው አትችሉም።

ሁሉም ዜጎች በብልጽግና የግፍ አገዛዝ የተንገሸገሹበት ሁኔታና ወቅት ላይ ስለምንገኝ፣ ማንኛውም የተሳሳተ የባልሥልጣናት እርምጃ ሀገራችንን ለከባድ አደጋ ስለሚያጋልጣት፣ ሁሉም ሀገር-ወዳድ ኢትዮጵያዊ የብልጽግናን የጅልና የግፍ ተግባሮች በጋራ ሊያስቆም ይገባል እንላለን። አንድነት ፍቱን መድሃኒት ነውና ሁሉም በጋራ ሊቆምና ወገኑንና ሀገሩን ሊታደግ ይገባል፣ ወቅቱም አሁን ነው እንላለን።

በሳሉና ሀገር-ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ በጋራ ትግሉ ሁሌም ያሸንፋል!!

አለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ትብብር ንቅናቄ።

Ethiopian Solidarity Movement
የኢትዮጵያውያን ትብብር ንቅናቄ
info@ethiosolidaritymovement.org
Phone: +1 (202) 754-5328
https://www.ethiopiansolidaritymovement.org

*የሚከተሉትን የማኅበራዊ መገናኛ ምንጮች አገናዝበናል።*

*References*

· AfricaPulse. (2025, April 9). Ethiopia: Ethiopian Health Workers Launch Campaign for Fair Pay, Insurance. https://www.africapulse.com/2025/04/09/ethiopia-ethiopian-health-workers-launch-campaign-for-fair-pay-insurance/

· AllAfrica. (2025, May 7). Ethiopian Health Professionals Association Urges Govt to Promptly Respond to Health Workers' Demands Amid Pre-Strike Demonstrations. https://allafrica.com/stories/202505070445.html

· EthioExplorer. (2025, April 8). Ethiopian health workers launch campaign for fair pay, insurance: threaten strike over unmet demands. https://www.ethioexplorer.com/ethiopian-health-workers-launch-campaign-for-fair-pay- insurance-threaten-strike-over-unmet-demands/

· Ethiopanorama. (2025, May 5). Ethiopia: 'We Are Prepared to Take Appropriate Legal Measures': Ethiopian Health Workers Issue Ten-Day Ultimatum to Ministry. https://ethiopanorama.com/?p=276347

· Borkena. (2025, February 21). The Exodus of Highly Specialized and Skilled Ethiopian Doctors: A Crisis That Demands Immediate Action. https://borkena.com/2025/02/21/the-exodus-of-highly-specialized-and-skilled-ethiopian- doctors-a-crisis-that-demands-immediate-action/

Ambassadors Media. (2025, April 9). Health workers launch campaign in Ethiopia. https://ambassadorsmedia.com/international-news/health-workers-launch-campaign-in-